# መኢአድ አገር አቀፍ የመስክ እንቅስቃሴውን አስመልክቶ ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጠ

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) የመስክ ተግባራዊ እንቅስቃሴውን በማስመልከት የፓርቲው ከፍተኛ አመራሮች ህዳር 16 ቀን 2001 ዓ.ም ለጋዜጠኞች ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጡ፡፡ በቃል ከተሰጠው መግለጫ በተጨማሪም የጽሁፍ መግለጫም ለጋዜጠኞች ተሰራጭቷል፡፡

ከምርጫ 97 በኋላ መኢአድ በሁሉም የኢትዮጵያ ክልሎች ሕጋዊና ሰላማዊ በሆነ መንገድ ለመንቀሳቀስ ወሰኖ ጽ/ቤቶችን መክፈቱንና ጽ/ቤቶች ባልተከፈቱባቸው አካባቢዎች ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴዎችን በማቋቋም መዋቅሩን በመዘርጋት ላይ መሆኑን ከፓርቲው መግለጫ መረዳት ተችሏል፡፡ ስለሆነም ባሁኑ ወቅት በብዙ ዞኖች ተከታታይ ሕዝብ የማደራጀት ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛሉ፡፡ ድርጅቱ በዞን ደረጃ ከሰላሳ በላይ ጽህፈት ቤቶችን በመክፈት እየተንቀሳቀሰ መሆኑንና ሌሎች ቢሮዎችንም ለመክፈት በሚቻልበት ሁኔታ ላይ የመስክ ግምግማውን ካደረጉ አባላት ጋር ሰፊ ውይይት ማድረጋቸውን ሃላፊዎቹ ጠቅሰው ከምርጫ 97 ጋር በተያያዘ በተለያዩ ቦታዎች ከድርጅቱ ቢሮዎች የተለያዩ ንብረቶች ተዘርፈው የተወሰዱ መሆናቸውንና ለማስመለስም ከሚመለከተው አካል ጋር ውይይት እያደረጉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በመቀጠልም በሰሜን፣ በደቡብ፣በምስራቅና በምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ከዞን እስከ ቀበሌ ድረስ ቢሮዎችን በመክፈት የማስተማር፣ የማደራጀትና የመቀስቀስ ሥራ በተጠናከረ መልኩ እየተከናወነ መሆኑን በመግለጫቸው አስረድተዋል፡፡

ነገር ግን መንግስት በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ በአባሎቻችን ላይ ጥቃት እያደረሰብን ነው ሲል የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ገለጿል፡፡ የድርጅቱ ምክትል ፕሬዝዳንት የምስራቅ ኢትዮጵያ ቀጠና ሀላፊ የሆኑት ሻለቃ ጌታቸው መንግስቴ እንደተናገሩት የመስክ ጉዞውን ካደረጉት በርካታ አባላት መካከል ከስድስት በላይ የስራ አስፈጻሚና የላዕላይ ምክር ቤት አባላት ላይ የማሰርና የማንገላታት ሁኔታ ደርሶባቸዋል ብለዋል፡፡

ከዚህም ሌላ አባላቱ ያረፉበት ሆቴል ድረስ በመሄድ በድርጅቱ ሰነዶች ላይ የመንግስት ታጣቂዎች ዘረፋ የፈጸሙባቸው መሆኑንም ጨምረው አስረድተዋል፡፡



ሻለቃ ጌታቸው መንግሥቴ መግለጫውን ሲሰጡ

ከህግ ውጪ የሚፈጸም የማሰርና የማንገላታት ስራ እንዲሁም የፓርቲውን ተወካዮች በየጊዜው ያለአግባብ እየጠሩ የሚፈጸምባቸው ማስፈራራት አሁንም እንደቀጠለና በእስር ላይ የሚገኙ የተወሰኑ የድርጅቱ አባላት አሁንም አለመፈታታቸውን አስታውቀዋል፡፡

ባንዳንድ አካባቢዎች በጽ/ቤቶቻችን ላይ የተሰቀሉትን ሰንደቅ አላማዎች በማውረድና ታፔላዎችን በመንቀል ህገ መንግስቱን በሚጻረር መልኩ ህገ ወጥ ተግባር እየተፈጸመባቸው በመሆኑ ድርጅቱ እያደረገ ያለውን የማደራጀት ስራ ላይ እንቅፋት መፍጠሩን ምክትል ፕሬዝዳንቱ ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም ይህ በጸጥታ ኃይሎች እየተፈጸመ ያለው ህገ ወጥ ተግባር ህገ መንግስቱን የሚጥስና የሚረግጥ አሳዛኝ ተግባር ነው ብለዋል፡፡



በአሁኑ ወቅት የተከሰተውን የኑሮ ውድነትን በተመለከተ የድርጅቱ ምክትል ፕሬዝዳንት የደቡብ ኢትዮጵያ ቀጠና ኃላፊ የሆኑት ዶ/ር ታዴዎስ ቦጋለ እንደገለጹት ፓርቲው ያለውን አመለካከት ሲያስረዱ መንግስት የህዝቡን ጩኸት በማዳመጥ ለችግሩ መፍትሔ ከመፈለግ ይልቅ የችግሩን መጠንና ስፋት ከዜጎችና ከዓለም ህብረተሰብ በመደበቁ

ህዝቡ በረሃብና በችግር እንዲጎዳ ማድረጉንና መንስዔውም ከመልካም አስተዳደር እጦት የመጣ ሰው ሰራሽ ችግርና ሊወገድ የሚችል መሆኑን ተናግረዋል፡፡ በተጨማሪም በብዙ ከተሞች እየታየ ያለው የውሃ፣የመብራትና የስልክ መቋረጥ አንዱ የአስተዳደር ችግር ነው በማለት አስታውቀዋል፡፡




የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት የሚከተለው የሊብራል ዲሞክራሲ ስርዓት ነው ያሉት የድርጅቱ ምክትል ፕሬዝዳንት የምዕራብ ኢትዮጵያ ቀጠና ኀላፊ የሆኑት አቶ አሰፋ ሀብተወልድ ሌሎች የዓለም ሀገራት የደረሱበት ስልጣኔ ነፃ የሆነ ምርጫ ለእድገታቸው ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ በሀገራችን ውስጥ የተከሰተው ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና የጤና ችግሮች የመልካም አስተዳደር እጦት ውጤቶች ናቸው ብለዋል፡፡




በመግለጫውም ላይ የፓርቲው የህዝብ ግንኙነት ኮሚቴ ኃላፊ የሆኑት ወ/ሪት መሰበወርቅ ቅጣው ከፊታችን ሀሙስ ህዳር 18 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ህዳር 21/2001 ዓ.ም ድረስ ለኢትዮጵያ ትንሳኤ ለማምጣት በሚል ዓላማ በመላው አዲስ አበባ የሰላማዊ ትግል ጥሪ መኢአድ ለህዝቡ እንደሚያደርግ ገልጸዋል፡፡

ወ/ሪት መሰበወርቅ ቅጣው



የሰላማዊ ትግል ጥሪውን በመዲናዋ የተለያዩ ሥፍራዎች በመኪና በመንቀሳቀስ እንደሚያካሂዱ የገለፁት ወ/ሪት መሶበወርቅ ቅጣው ከ60 ሺ በላይ በራሪ ወረቀቶች እንደሚሰራጩ፣በሲዲ የተቀረፁ የድምጽ መልእክቶችን እንደሚተላለፍና ‹‹ሞረሽ›› በተባለው የፓርቲው ኪነት ቡድን በሙዚቃና በውዝዋዜ የተደገፈ ቅስቀሳ እንደሚካሄድ አስታውቀዋል፡፡

--